# ነውና ነግ በኔ ጭጭ አትበል ወገኔ

የትግሬው ነጻ አውጭ (“ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ”)

እንዲያመቸኝ ብሎ

ለመግዛት ከፋፍሎ

ከሃያ ዓመት በፊት፤

ለንደን ከተማ ውሥጥ እንዲያ ሲደራደር

የኤትዮጵያ ነጻ አውጭ ምን አቀረበለት?

ውያኔ  ተቀምጦ በነጭ ፈረስ ላይ

ምብትን ሲያከፋፍል

ለጎጠኛው ሁሉ

እንዲት ቢያታለው ነው

ከሃያ ዓምት ኋላ እንዲህ የፈነዳው?

## እባክህ አዳምጠኝ ነውና ነግ በኔ፤

## በቃ በለው ዛሬ፣ ጭጭ አትበል ወገኔ!

ያ “ወያኔ ሓርነት ትግራይ”

በለንደን ከተማ እንዲያ ሲደራደር

የተራቆተውን በድህነት ይዞት፣

በጎሣ ከፋፎሎ አዋጅ በማስመታት፤

እንዲህ አትቶለት፤

ከዛሪ ጀምሮ ላንተ ይሁንልህ፣ መንደርህ፣ አገርህ፤

ወርቁም  ጎሣ ያንተ አማራም ጠላትህ።

እንዴት ቢያታለው ነው

ከሃያ ዓምት ኋላ ፍሪውን ይጨደው?

**ካለፈው ተምረን ዛሬ እንነሣ፤**

**የሰው መብቱ ይቅደም አንተምን በጎሣ።**

አዳምጠኝ ወልቃይት ሌላው ይቅርና

አዳምጠኝ ነቀምቴ ሌላው ይቅርና

አረ ተው ጭጭ አትበል ኢትዮጵያ ወገኔ፤

እንዲህ ከቀጠለ በልምድም ከሆነ

አይቀርም ነግ በኔ።

© ለምለም ፀጋው፣ ሚያዝያ 26፣ 2006 (May 4, 2014)

በ አምቦና በሌሎች ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣታቸው ለተገደሉት ሁሉ መታሰቢያ የተጻፈ. ሁናቲውን ከታች በተዘረዘሩት ድረ ገጾች ያንብቡ።

http://www.ethiomedia.com/16file/4546.html

http://www.ethiograph.com/video/watch.php?vid=ce944354f

http://ecadforum.com/News/olf-press-release-on-tplfs-mass-killings-of-the-oromo-students